የምርጫ አለመግባባት አፈታት ሂደት በኢትዮጵያ

የምርጫ አለመግባባት ዓይነቶች

- በምርጫ ሂደት የተለያዩ ደረጃዎች ውስጥ ሊነሱ የሚችሉ በርካታ የቅሬታ፣ ክርክር እና የሥነ ምግባር ደንብ ጥሰት አይነቶች አሉ፡

❖ በምርጫ ተወዳዳሪዎች መካከል ወይም

❖ በምርጫ ተወዳዳሪዎች እና በምርጫ አስፈጻሚዎች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶችን ፣

❖ የተለያዩ ከምርጫ ጋር የተያያዙ ዝግጅቶች፣ አሠራሮች እና ማስፈጸሚያ ዘዴዎች ጋር የተዛመዱ የአስተዳደር ጥሰቶችን ወይም ብልሹ አሠራሮችን፣

❖ የሥነ ምግባር ደንቦች ወይም የስነምግባር ተግባራት ጥሰቶችን ፣

❖ የውጤት ተቃውሞዎችን ፣ እና ከምርጫ ጋር የተያያዙ የወንጀል ጥፋቶችን ሊያካትቱ ይችላሉ።

በአጠቃላይ የተለያዩ የክርክር እና የቅሬታ ዓይነቶች በቅድመ ምርጫ፣ በምርጫ ቀን፣ እና በድህረ-ምርጫ የሚከሰቱ ተብለው ሊከፈሉ ይችላሉ።



የቅድመ-ምርጫ አለመግባባቶች

☞ በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 የተካተቱ የቅድመ-ምርጫ አለመግባባቶች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ ፥

- በመራጮች ምዝገባ ወቅት ወይም ከመራጮች መዝገብ ጋር በተያያዘ የሚነሱ ቅሬታዎች (የምርጫ ጣቢያ የምርጫ አስፈፃሚዎች መራጮች እንዳይመዘገቡ የወሰኑትን ውሳኔ በመቃወም ፣
- ወይም ተመዝጋቢው የዜግነት፣ የነዋሪነት ወይም ሌሎች በመራጭነት ለመመዝገብ ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶችን ባለማሟላቱ መመዝገብ የለበትም የሚሉ ቅሬታዎች ፣ ወይም አንድ መራጭ ከአንድ ጊዜ በላይ ተመዝግቧል የሚል ቅሬታ) (አንቀጽ 152)

ቅድመ ምርጫ የቀጠለ...

- በእጩ ምዝገባ ወቅት የሚነሱ ቅሬታዎች (በምርጫ ክልል ጽህፈት ቤት የምርጫ አስፈፃሚዎች አንድ ሰው እንደ እጩ እንዳይመዘገብ የወሰኑትን ውሳኔ በመቃወም ፣
- ወይም ተመዝጋቢው ዕድሜ፣የዜግነት፣ የነዋሪነት ወይም ሌሎች በእጩነት ለመመዝገብ ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶችን ባለማሟላቱ መመዝገብ የለበትም የሚሉ ተቃውሞዎች) (አንቀጽ 153 (1) እና (2))
- ከፖለቲካ ፓርቲ ምዝገባ ጋር በተያያዘ የሚነሱ ቅሬታዎች (ምርጫ ቦርድ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ እንዳይመዘገብ የከለከለበትን ውሳኔ በመቃወም
- ወይም የፖለቲካ ፓርቲው የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ መስፈርቶችን ለምሳሌ የድጋፍ ፊርማ ባለማሟላታቸው የፖለቲካ ፓርቲ ምዝገባ እንዳይደረግ የሚቀርቡ ተቃውሞዎች) (አንቀጽ 68) (3)) እና (አንቀጽ 69 (2))

ቅድመ ምርጫ የቀጠለ---

☞ በሕዝብ ሀብት ላይ አላግባብ መጠቀምን፣ ስም ማጥፋትን ፣ ዓመፅን የሚያነሳሱ እና የሥነ ምግባር ደንቡን የሚጥሱ መግለጫዎችን ጨምሮ ሕገ-ወጥ የምርጫ ዘመቻ/ቅስቀሳ (አንቀጽ 129 ፣132-136 ፣ 142-147)

የምርጫ ቀን አለመግባባቶች

በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 የተካተቱት በምርጫ ቀን ሊነሱ የሚችሉ ክርክሮች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ ፣

- ሌላን ሰው መስሎ መቅረብን (impersonationን) (አንቀጽ 54(1
- ከአንድ ጊዜ በላይ መምረጥን (አንቀጽ 50 (2))

የምርጫ ቀን አለመግባባቶች የቀጠለ...

- የድምጽ አሰጣጡን ሚስጢራዊነት አለማክበርን (አንቀጽ 121 (8) (ለተወካዮች)፣ 130 (4) እና 143 (11))
- በምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ የሚደረግ ህገ ወጥ የምርጫ ቅስቀሳን (አንቀጽ 157 (2) እና (3) (ረ))
- የድምፅ አሰጣጡ ሂደት ግድፈቶች ነበሩበት የሚሉ ቅሬታዎች ፣
- በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 ክፍል 6 ላይ የተዘረዘሩ ሌሎች ጥሰቶችን ይመልከቱ።
- የአንድን ሰው የመምረጥ መብትን በሚነፍጉ ውሳኔዎች ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎች ወይም የአንድን ሰው የመምረጥ መብት የሚቃወሙ አቤቱታዎች (አንቀጽ 54፣ 154 (1) እና (5))
- ጥቃትን ፣ ዛቻዎችን እና/ ወይም ማስፈራራትን በተመለከተ የሚቀርቡ ቅሬታዎች (አንቀጽ 98(1)(ረ) ፣ 121 (7) (ለወኪሎች)፣ 134 ፣ 142 (5) ፣ 144 ፣ 147፣ 157 (4) (ሐ) እና 159)

የምርጫ ቀን አለመግባባቶች የቀጠለ...

- በምርጫ ቀን የምርጫ ተግባራት ለመገናኛ ብዙሃን (አንቀጽ 123 ፣ 126 እና 146 (1) እና (2)) ፣ ለታዛቢዎች (አንቀጽ114(1) ፣ 116 እና 146 (3)) ወይም ለወኪሎች (አንቀጽ 120 እና 122 (2)) ተደራሽ እንዳይሆኑ ተደርጓል
- በጸጥታ አስከባሪዎች ጣልቃ ገብነት ነበር የሚሉ ቅሬታዎች (አንቀጽ 48 (5) እና (6) ፣ 135 (1) እና (2) እና በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 ክፍል 6 ውስጥ የተጠቀሱ ሌሎች ጥሰቶች)

የድህረ-ምርጫ ቀን አለመግባባቶች

ከምርጫ ቀን በኋላ የሚነሱ አለመግባባቶች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ (አንቀጽ 58 (6) ፣ 60 (1) ፣ 62 (2) ፣ 131 (2) እና አዋጅ 1162/2011 አንቀጽ 155 የተዘረዘሩትን)

- የድምፅ ቆጠራው ግድፈቶች ነበሩበት የሚሉ ቅሬታዎች
- የውጤት ማዳመርና ማስተላለፍ ሂደቱ ግድፈቶች ነበሩበት የሚሉ ቅሬታዎች
- የውጤት ይፋ አደራረግ ሂደቱ ግድፈቶች ነበሩበት የሚሉ ቅሬታዎች

ሌሎች አለመግባባቶች

- የፖለቲካ ፓርቲ ውስጣዊ አለመግባባቶች (አንቀጽ 74 (6))
- በፓርቲዎች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች (ከምርጫ ሂደት ጋር በተያያዙ የፓርቲዎች አለመግባባቶች) (አንቀጽ 151 (1-4)

የአለመግባባት አይነቶች

- ከምርጫ ጋር በተያያዙ የሚነሱ አለመግባባቶች(electoral disputes)
- አስተዳደራዊ አለመግባባቶች **(Administrative Disputes)**
- የሥነ ምግባር ጥሰቶች**(Ethical violations)**
- የምርጫ ውጤት አለመግባባቶች **(Results disputes or petitions)**
- ጥፋቶች ወይም የወንጀል ድርጊቶች **(Election offences or crimes:)** ተብለው ሊከፋፈሉም ይችላሉ።

ከምርጫ ሂደት ጋር በተያያዘ ለፍርድ ቤት የሚቀርቡ የጉዳይ አይነቶች(categories of complaints)

- በመራጮች ምዝገባ ሂደት የሚነሱ ክርክሮች (አንቀጽ 152)
- በዕጩዎች ምዝገባ ሂደት የሚነሱ ክርክሮች (አንቀጽ 153)
- በድምፅ አሰጣጥ ሂደት ስለሚነሱ ክርክሮች (አንቀጽ 154)
- ከድምፅ ቆጠራና ዉጤት ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክርክሮች (አንቀጽ 155)
- ከዕጩዎች ምርጫ መለያ ምልክት ጋር በተያያዘ (አንቀጽ 37/7፣ አዋጅ ቁጥር 1133/2011- አንቀጽ 17/1)
- የስነ ምግባር ጥሰቶችን በሚመለከት (አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 149 እና 150)
- ከፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ቅሬታዎች

- ጥፋቶችና የወንጀል ድርጊቶች (breach of code of conduct and electoral offences)

የምርጫ አለመግባባቶችን ለመፍታት ሥልጣን ያላቸው አካላት

ከላይ የተዘረዘሩትን የአለመግባባት አይነቶች ለመፍታት በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 ስልጣን የተሰጣቸው አካላት የሚከተሉት ናቸው፥

- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
- በተለያዩ ደረጃዎች ያሉ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች
- የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ መድረክ *(አማራጭ የክርክር አፈታት/ Alternative Dispute Resolution (ADR))
- የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት *(አማራጭ የክርክር አፈታት/ Alternative Dispute Resolution (ADR))
- ስልጣን ያላቸው የፌዴራል እና የክልል ፍርድ ቤቶች

- ☞ከምርጫ ሂደት ጋር በተያያዘ ወደ ፍርድ ቤት የሚቀርቡ ጉዳዮች የሚመሩበት የሥ/ሥርዓት እና የማስረጃ ደንብ

የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ደንብ

☞አዋጅ ቁጥር 1162/2011 ከምርጫ ሂደት ጋር በተያያዘ የሚነሱ የሥርዓቶች እንዲሁም ቅሬታዎችን ተቀብለዉ እልባት የሚሰጡ አካላትን ለይቶ ይደነግጋል።

- በዚህም መሠረት የምርጫ ጣቢያ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ፣ የምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ፣ ክልል ቅ/ጽ/ቤት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ እና የምርጫ ቦርድ ከምርጫ ሂደት ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን አይቶ ለመወሰን ስልጣን ተሰጥቶአቸዋል።
- በእነዚህ አካላት የተሰጠን የመጨረሻ ዉሳኔ (ዉሳኔ በተገቢዉ ጊዜ ባለመሰጠቱ ምክንያት አቤቱታ ለፍ/ቤት ሊቀርብ እንደሚችል በአዋጁ የተመለከተዉ እንዳለ ሆኖ) በመቃወም የሚቀርብን አቤቱታ ተቀብሎ የማየት ስልጣን የተሰጠዉ ለፍርድ ቤቶች ነዉ (የአዋጁ አንቀጽ 150-155 ድንጋጌዎች - ሌሎችም)።

- አዋጁ ለፍርድ ቤቶች በዚህ መልኩ የሚቀርቡላቸዉ ጉዳዮች መቼ እንደሚቀርቡ እና በምን ያህል ጊዜ ዉስጥ ዉሳኔ ሊሰጥባቸዉ እንደሚገባ (ለሁሉም ባይሆንም) በተለያዩ ድንጋጌዎቹ ያስቀምጣል።
- ይሁንና የምርጫን መሠረታዊ ባህሪ መሠረት ባደረገ መልኩ ፍርድ ቤቶች ክርክሩን እንዴት ባለ ሁኔታ መምራት እንዳለባቸዉ ዝርዝር ሁኔታዎችን አያስቀምጥም።
- በሌላ በኩል ከምርጫ ጋር በተያያዘ ለፍርድ ቤት የሚቀርብ ክርክር ከጊዜ እና ከሌሎች ምክንያቶች አንፃር የምርጫን ልዩ ባህሪ ባገናዘበ መልኩ ሊመራ ይገባል።
- ይህን የሥ/ሥርዓት ደንብ ማዉጣት ያስፈለገበት ምክንያትም ይሄዉ ነዉ።

የደንቡ ይዘት

- ጠቅላላ ድንጋጌ
- ከምዕራፍ ሁለት እሰከ ሰባት - ከምርጫ ሂደት ጋር በተያያዘ ወደ ፍርድ ቤት የሚመጣ እያንዳንዱ ጉዳይ የሚመራበትን ሥ/ሥርዓት እና በፍርድ ቤት የሚሰጥ ዉሳኔ በዝርዝር የያዘ ነዉ።
- ምዕራፍ ስምንት - የአመራር ስርዓት - የአቤቱታ/የመልስ ይዘት፣ የረጂስትራር ሚና፣ አቤቱታዉን በመመርመር ረገድ ችሎት ስላለዉ ስልጣን፣ ስለመጥሪያ አደራረስ እና የተጠሪ ያለመቅረብ ስለሚያስከትለዉ ዉጤት እና ሌሎች ጉዳዮችን የያዙ 13 አንቀፆች ያሉት ነዉ።
- የመጨረሻዉ ምዕራፍ - ልዩ ልዩ ድንጋጌዎችን የሚመለከት ነዉ።

የደንቡ ዓላማ

- ✓ ከምርጫ ሂደት ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክርክሮች ካላቸው ባህርያት አንጻር በልዩ ሁኔታ የሚስተናገዱበትን፤
- ✓ ጉዳዮች በአጭር ጊዜ ውስጥ እልባት የሚያገኙበትን እና ባለጉዳዮች በእኩልነት የመሰማት ሕገ መንግስታዊ መብታቸው የተከበረ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥነ ሥርዓት የመዘርጋት ናቸዉ፡

በዚህ ደንብ የሚሸፈኑ ጉዳዮች፡

- በመራጮች ምዝገባ ሂደት የሚነሱ ክርክሮች (አንቀጽ 152)
- በዕጩዎች ምዝገባ ሂደት የሚነሱ ክርክሮች (አንቀጽ 153)
- በድምፅ አሰጣጥ ሂደት ስለሚነሱ ክርክሮች (አንቀጽ 154)
- ከድምፅ ቆጠራና ዉጤት ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክርክሮች (አንቀጽ 155)
- ከዕጩዎች ምርጫ መለያ ምልክት ጋር በተያያዘ (አንቀጽ 37/7፣ አዋጅ ቁጥር 1133/2011- አንቀጽ 17/1)
- የስነ ምግባር ጥሰቶችን በሚመለከት (አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 149 እና 150)
- ከምርጫ ሂደት ጋር በተያያዙ ሌሎች ጉዳዮች ላይ በቦርዱ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ስለሚቀርብ አቤቱታ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

- ለፍርድ ቤት የሚቀርቡ አቤቱታዎች የሚስተናገዱበትን አግባብ <u>የአቤቱታ አቀራረብና ውሣኔ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት</u> የሚል ርዕስ ተሰጥቶአቸዉ በደንቡ ከአንቀጽ 5 ጀምሮ እስከ 30 ድረስ ተደንግገዋል።
- እያንዳንዱ ጉዳይ ከይዘት፣ ጉዳዩ በመጀመሪያ ከሚስተናገድበት ተቋም እንዲሁም እንደየጉዳዩ ባህርይ አቤቱታ የሚቀርብበት እና እልባት እንዲያገኝ የሚጠበቅ ጊዜ የተለያየ በመሆኑ ምክንያት እያንዳንዱ ጉዳይ የየራሱ ምዕራፍ ተሰጥቶት በተለያዩ አንቀጾች እና ንዑሳን አንቀፆች እንዲቀረጽ ተደርጓል።
- ጠቅላላ ድንጋጌዎች ከምርጫ ጋር በተያያዘ ለሚቀርቡ በዚህ ደንብ ለተሸፈኑ ጉዳዮች ሁሉ ተፈፃሚ የሚሆኑ የጋራ ድንጋጌዎች ናቸዉ።

☞ የተወሰኑትን ለማየት ያህል፦

1. **የሬጂስትራር ኃላፊነት** - አቤቱታው በየደረጃው የታየ መሆኑን፣ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የቀረበ መሆኑን፣ የምስክሮች ቃል ተመዝግቦ ከሆነ የምስክሮቹ ቃል የተመዘገበበት ሰነድ መቅረቡን፣ ሰነዶች በፍርድ ቤቱ የሥራ ቋንቋ ተተርጉመው መቅረባቸውን፣ ወኪል ለመሆን የተፈቀደለት ሰው የውክልና ማስረጃ ማቅረቡን፣ የሚመለከታቸው አካላት ዘንድ አቅርቦ ውሳኔ ሳያገኝ የቀረ ከሆነ ይህንኑ ያረጋገጠበት ቃለ መሃላ መቅረቡን የማረጋገጥ ኃላፊነት (ሌሎች ቴክኒካል ብቃት ማረጋገጥ እንደ ተጠበቁ ሆነዉ)
2. **አቤቱታዉን ስለመመርመር** - አቤቱታው ወዲያዉኑ ለችሎት መቅረብ እንዳለበት፣ አቤቱታዉ ምክንያት ያለዉ መሆን ያለመሆኑን መርምሮ ምክንያት ከሌለዉ መሰረዝ፤

ጠቅላላ ድንጋጌ የቀጠለ...

3. መጥሪያ አደራረስ - በአካል ማድረስ አለበት

አመልካቹ መጥሪያ ወዲያውኑ ከፍርድ ቤቱ አለመውሰዱ ከተረጋገጠ ወይም መጥሪያውን ያለ በቂ ምክንያት ለተጠሪ ሳያደርስ የቀረ እንደሆነ ወይም ተጠሪው መልስ ለማቅረብ በማይችልበት በተጣበበ ጊዜ ውስጥ የሰጠው እንደሆነ አመልካች ጉዳዩን ለመከታተል እንዳልፈለገ ተቆጥሮ አቤቱታው ውድቅ ይደረጋል፤ መዝገቡ ይዘጋል።

4. ተሳታፊ ስለሚሆኑ ሰዎች - መግባት የሚገባዉን ወይም ያገባኛል የሚል ሲኖር ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ መስጠት ይችላል።

5/ ጉዳዮችን ስለማጣመር - ከባለጉዳዮቹ አንደኛው ወገን ባመለከተ ጊዜ ወይም ፍርድ ቤቱ ተገቢ ነው ብሎ ሲያምን እና ውሳኔውም በዚህ ደንብ በተመለከቱት ውሳኔ የመስጫ ጊዜያት ውስጥ ሊሰጥ የሚችል መሆኑን ሲገነዘብ ጉዳዮቹ ተጣምረው በአንድነት እንዲታዩ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል።

6/ የክርክር አመራር ሥርዓት፡- አቤቱታና መልስ መርምሮ ወዲያዉኑ ዉሳኔ ይሰጣል (መርህ)፤ ውሳኔ ላይ ለመድረስ እንደማይችል ሲረዳ አስፈላጊ ነው ብሎ ያመነውን ማስረጃ እና ምስክር ብቻ አስቀርቦ ወይም ሰምቶ ውሳኔ ይሰጣል ።(በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 241 ላይ የተደነገገው የክስ መስማት ሥርዓት ተፈጻሚ የሚሆነው በልዩ ሁኔታ ነው።)

7. አቤቱታ እና መልስ ስለማሻሻል -በመርህ ደረጃ የተከለከለ ነዉ።

ልዩ ሁኔታ(exception)- ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት የሚያስፈልግ ነው ብሎ ሲያምን እና ውሳኔውም በዚህ ደንብ በተመለከቱት ውሳኔ የመስጫ ጊዜያት ውስጥ ሊሰጥ የሚችል መሆኑን በማገናዘብ

የቀጠለ

8. የማስረጃ አቀራረብ - ግራ ቀኝ ያቀረባቸዉን ማስረጃዎች የሚቀበለዉ አስፈላጊነታቸዉ ከታመነበት ብቻ ነዉ፤ በእራሱ አነሳሽነትም ሊያዝ ይችላል።

9 የዉሳኔ ይዘት - (ልዩ)- የውሳኔውን ቅጂ ለተከራካሪ ወገኖች ይሰጣል፤ እንዲፈጸም እንደአስፈላጊነቱ ለቦርዱ፣ ለክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቱ፣ ለምርጫ ክልሉ፣ ለምርጫ ጣቢያው ወይም ለሌላ ለሚመለከተው አካል ትዕዛዝ ይሰጣል።

10 አፈፃፀም - ውሳኔ የደረሰው አካል ወዲያውኑ በውሳኔው መሰረት የመፈጸም ግዴታ እንዳለበት፤ የአፈጻጸም አቤቱታዉም ጉዳዩን በተመለከተው ችሎት እና ጉዳዩ በታየበት መዝገብ ላይ መስተናገድ እንዳለበት ተመልክቷል።

የቀጠለ

11 **የቀጠሮ አሰጣጥ፦**በዚህም መሠረት የቀጠሮ አወሳሰንን በሚመለከት ድንጋጌ (አንቀጽ 45) ማናቸውም ፍርድ ቤት ማናቸውንም አይነት ትዕዛዝ ሲሰጥ የምርጫ የጊዜ ሰሌዳ እና የምርጫ ጉዳዮችን ልዩ ባህሪያት ከግምት ማስገባት እንደሚኖርበት፤ በደንቡ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ጉዳዮችን የማስተናገድ፤ ተለዋጭ ቀጠሮ መስጠት የሚቻለዉ በዚህ ደንብ በተመለከቱት ውሳኔ የመስጫ ጊዜያት ውስጥ ውሳኔ መስጠት የሚችል መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ መሆኑን ይደነግጋል።

12 **አጣዳፊ ጉዳዮች** – ቅድሚያ ሊሰጣቸዉ እንደሚገባ

የቀጠለ

13 ፎርሞች፡_ የክርክር ሂደቱን ለማቀላጠፍ አጋዥ መሣሪያ ነዉ በሚል እሳቤም ፎርምን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች እንዲካተቱ ተደርጓል በዚህም መሰረት የሚቀርቡ አቤቱታዎች፣ መልሶች፣ በፍርድ ቤት የሚሰጡ ትዕዛዞች፣ ፍርዶች ወይም ውሳኔዎች እና ሌሎች ሰነዶች የሚጻፉበትን ፎርሞች የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሊያዘጋጅ ይችላል፤ ፍርድ ቤቶች፣ ተከራካሪ ወገኖች እና ሌሎች በሚዘጋጁት ፎርሞች መገልገል እንዳለባቸው፤ ነገር ግን ፍርድ ቤቶች በዚህ ደንብ የተዘጋጁትን ፎርሞች መጠቀም የማያመች ሆኖ ያገኙት እንደሆነ የራሳቸውን ፎርሞች መጠቀም ይችላሉ።

የቀጠለ

14 ጉዳዮች የሚሰተናገዱባቸው ቀናት፡_

- ጉዳዮች በፍርድ ቤት የሚሰተናገዱባቸዉን ቀናት በተመለከተም ደንቡ ልዩ ድንጋጌ ይዟል። ለዚህም ምክንያት በምርጫ ሂደቱ የሚከናወኑት ተግባራት በጊዜ የተገደበ ነዉ። በተወሰነዉ ጊዜ ዉስጥ ለጉዳዩ ዉሳኔ መስጠት ካልተቻለ ክርክሩ ዉጤት አልባ ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል።
- በዚህም መሠረት ፍርድ ቤቶች ቅዳሜ፣ እሁድ እንዲሁም በህዝብ በዓላት ቀን ጉዳዮችን ማየት እንደሚችሉ፤ በዚህ መልኩ የሚሰተናገዱ ከሆነ የፍርድ ቤት አስተዳደር ለዳኞች እና ለሌሎች ሰራተኞች አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶችን የማቅረብ ግዴታ እንዳለበት ረቂቅ ደንቡ ይደነግጋል።

የቀጠለ

15 ውክልና፣

- በውክልና ከመከራከር ጋር በተያያዘ የምርጫ ሂደትን አስመልክቶ በሚደረግ ክርክር ተካፋይ ሊሆን የሚችለዉን ሰዉ ማንነት መሠረት ባደረገ መልኩ በተለየ ሁኔታ ማየት በማስፈለጉ እራሱን የቻለ ድንጋጌ በደንቡ እንዲካተት ተደርጓል (አንቀጽ 48)።
- በዚህም መሰረት መራጭ ከመሆን የተከለከለ ሰው ከሆነ እራሱ ወይም በጠበቃው፣ የግል ዕጩ ተወዳዳሪ ከሆነ በጠበቃው ሆኖ የፖለቲካ ፓርቲ ዕጩ ተወዳዳሪ ከሆነ ግን በጠበቃው ወይም በወከለው የፖለቲካ ፓርቲ ኃላፊ ወይም የፖለቲካ ፓርቲው በወከለው ሰው፣ የፖለቲካ ፓርቲ ከሆነ የፖለቲካ ፓርቲ ኃላፊ ወይም ኃላፊው የወከለው ሰው ወይም በጠበቃው ብቻ መሆን እንዳለበት ተመልክቷል።

የቀጠለ

16 አቤቱታና ውጤቱ፦ በጊዜው ያልቀረበ አቤቱታ ተቀባይነት የለዉም።

17 ሥለ ድጋሚ ዳኝነት፦

- የምርጫ ጉዳዮችን ክርክር መሠረታዊ ባህርይ ያላገናዘበ እና የተራዘመ ክርክር እንዲኖር በር ሊከፈት እንደማይገባ በማመን በፍርድ ቤት በሚሰጥ ዉሳኔ ላይ የተወሰነ ገደብ እንዲቀመጥ ተደርጓል።
- በዚህም መሰረት በፍርድ ቤት ታይቶ የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ ጉዳይ በድጋሚ ዳኝነት እንዲታይበት ጥያቄ መቅረብ አይችልም።

❖ **Exception** - ውሳኔው የተሰጠው በሀሰተኛ ማስረጃ መሆኑ ከተረጋገጠ እና ማስረጃው ውሳኔውን ሊያስቀይረው የሚችል ከሆነ እንዲሁም ጉዳዩን በአዋጁ በተቀመጠው የመወሰኛ ጊዜ መወሰን እንደሚቻል ፍርድ ቤቱ ካረጋገጠ

የቀጠለ

18 ጉዳይን መመለስ (Remand) የተከለከለ ሥለመሆኑ፦-ጉዳዮችን ተቀብሎ የሚያስተናግድ ፍርድ ቤት የሚሰጠው ውሳኔ **የመጨረሻ** ነው። ፍርድ ቤት ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ በማኛቸውም ሁኔታ ቢሆን በጉዳዩ ላይ አስቀድሞ ውሳኔ የሰጠው አካል በድጋሚ አይቶ እንዲወስን ሊመልስለት አይችልም።

ከዕጩ ምዝገባ በተያያዝ የሚቀርቡ ቅሬታዎች

የመብቱ የህግ መሰረት፡_

የሰብአዊ መብቶች ኮንቬንሽን

- **የአፍሪካ የሰብአዊ መብት ቻርተር**
- **የኢፌዴሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 38(1)**
- **አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 30-42 እና አንቀጽ 153**

የቀጠለ

☞ ዕጩ ሆኖ ለመመዝገብ የሚያስፈልጉ መስፈርቶች አዋጅ 1162/2011 አንቀጽ 31

- ✓ ኢትዮጵያዊ ዜጋ እና ለመምረጥ የተመዘገበ
- ✓ በምዝገባ ዕለት 21 ዓመት ወይም ከዛ በላይ የሆነው
- ✓ ከምርጫው ዕለት አስቀድሞ በምርጫ ክልሉ ውስጥ በመደበኝነት አንድ አመት ከኖረ ወይም የትውልድ ቦታው በዕጩነት ሊቀርብበት በፈለገበት የምርጫ ክልል ከሆነ
- ✓ መወዳደር የሚፈልግበት ከተማ ወይም መረዳ ከአንድ በላይ የምርጫ ክልሎችን የሚያቅፍ ከሆነ እና በከተማው ወይም በወረዳው ውስጥ ለሁለት ዓመት በመደበኝነት የሰራ ከሆነ በዚያው ከተማ ወይም መረዳው በፈለገው የምርጫ ክልል

ከዕጩ ምዝገባ የቀጠለ

- ✓ በሕግ ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብቱ ያልተገፈፈ
- ✓ በአዕምሮ ሕመም ምክንያት ለመወሰን ብቃት የሌለው መሆኑ ስልጣን ባለው አካል ወይም በበቂ ማስረጃ የተረጋገጠበት ካልሆነ
- ✓ ቦርዱ በዚህ አዋጅ መሰረት የሚያወጣውን የምርጫ ስነ ምግባር ደንብ ተቀብሎ ከፈረመ
- ☞ ዕጩው አንድ አመት መኖር እንደመመዘኛ ቀሪ የሚሆነው በስራ ወይም በትምህርት ምክንያት ከምርጫ ክልሉ ውጪ የነበረን ሰው ወይም ከዚህ በፊት በምርጫ ክልሉ ተመርጦ በመስራት ላይ ያለን ሰው አይመለከትም

ከዕጩ ምዝገባ የቀጠለ

የመንግስት ሰራተኞች (33)

☞ በግል ወይም የፖለቲካ ፓርቲ አባል በመሆን ለምርጫ መወዳደር ይችላል

☞ የምርጫ ቅስቃሳ በሚካሄድበት ወቅት እና ምርጫው በሚከናወንበት ግዜ ያለፍቃድ ደመወዝ እንዲሰጠው ይደጋል

☞ ሰራተኛው የቀጣሪውን የመንግስት መስሪያ ቤት ንብረት መገልገል አይጠበቅበትም

ከዕጩ ምዝገባ የቀጠለ

የዕጩዎች ልዩ መብት

☞ ከባድ ወንጀል ሲፈጽሙ እጅ ከፍንድ ካልተያዙ በስተቀር ምርጫው እስከሚጠናቀቅ በወንጀል ተጠርጥረው አለመያዝ

☞ ዕጅ ከፍንጅ ባይሆንም ሕጋዊ እርምጃ ሊወሰድባቸው የሚችለው የምርጫው ውጤት በቦርድ አማካይነት በይፋ ከተገለጸ በሃላ ነው

☞ አሸናፊው ሰው በምርጫው ወቅት በፈጸመው ወንጀል የሚጠየቀው በሚመለከተው ምክር ቤት የሕግ ከለላው ሲነሳ ብቻ ነው፡፡

ከዕጩ ምዝገባ የቀጠለ

☞ ዕጩ ሆነው መቅረብ የማይችሉ ሰዎች (33-3 እና 4)

✓ ዳኞች

✓ ዓቃቢ ሕጎች

✓ ወታደሮች

✓ ፖሊሲ

✓ የጸጥታ ኃይሎች

✓ የደህንነት ሰራተኞች

✓ የቦርድ ሰራተኞች

☞ ከፈለጉ ግን የያዙትን የመንግስት ስራ መልቀቅ አለባቸው፡፡

☞ ካልለቀቁ ግን ማንኛውንም ተወዳዳሪ ለማስመረጥ በመደገፍ፣ በመናገር፣ በመጻፍና በመሳሰሉት ተሳታፊ መሆን የለባቸውም፡፡

ከዕጩ ምዝገባ የቀጠለ

ለአቤቱታ ምክንያቶች

☞ በዕጩነት ከመመዝገብ መከልከል

☞ዕጩ ሆኖ ሊመዘገብ የማይገባው ሰው መመዝገብ

- ዕጩ ሆኖ ለመመዝገብ የተደነገጉ መስፈርቶች አለሟሟላት
- ዕጩ መሞት

ከዕጩ ምዝገባ የቀጠለ

ሊቀርቡ የሚችሉባቸው ደረጃዎች እና የሚቀርብበት ግዜ ፡-

☞ መጀመሪያ ደረጃ፡- የምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ (153(1) እና (2))

አቤቱታው ሊቀርብ የሚችለው ከእጩዎች የምዝገባ ቀን ጀምሮ የተመዘገቡ እጩዎች ይፋ እስከሚሆኑበት ቀን ድረስ ነው

ኮሚቴውም አቤቱታውን መርምሮ በ5 ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ውሳኔ ይሰጣል

ከዕጩ ምዝገባ የቀጠለ

☞ **የመጀመሪያ ክለሳ፡-** የክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት (153(5))

በምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ ቅሬታ ያለው ሰው በቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ለሚቋቋም ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በ5 ቀናት ቅሬታውን ማቅረብ አለበት

ኮሚቴውም በ 7 ቀናት ውስጥ ወሳኔውን በጽሑፍ ይሰጣል

☞ ሁለተኛ ክለሳ፡- (153(8)

የክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በ7 ቀናት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ ወይም ቅሬታ አቅርቢው በተሰጠው ውሳኔ ካልተስማማ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው

ችሎቱም በ15 ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል

ከዕጩ ምዝገባ የቀጠለ

ተመራጭ ልሆን ይገባል በሚል ሊቀርቡ ስለሚችሉ ማስረጃዎች

የዕጩው ዕድሜ፣ ማንነት እና የመኖርያ ቦታ

- ✓ ሕጋዊ እና ግዜው ያላለፈበት መታወቂያ ካርድ ፣ የመንጃ ፍቃድ፣
- ✓ የልደት ሰርቲፍኬት
- ✓ በምርጫ ክልሉ ለሁለት ዓመት የኖሩ መሆኑን የሚገለጽ የቅጥር ወይም ሌላ ማስረጃ
- ✓ የዕጩውን ዕድሜ ወይም ማንነት በሰነድ ማረጋገጥ ካልተቻለ በምርጫ ክልሉ ከአምስት አመት በላይ በቆዩ ሶስት ምስክሮች የሚሰጡት ቃል

ከዕጩ ምዝገባ የቀጠለ

ተመራጭ ሊሆን አይገባም በሚል ሊቀርቡ ስለሚችሉ ማስረጃዎች

- ✓ ኢትዮጵያዊ አይደለም፣
- ✓ ዕድሜው ከ21 ዓመት በታች ነው
- ✓ የነዋሪነት መስፈርት አላሟላም
- ✓ ሞቷል
- ✓ በማጭበርበር ተመዝግቧል
- ✓ ሁለቴ ወይም ከዛ በላይ ተመዝግቧል
- ✓ የአዕምሮ የጤና ሁኔታ
- ✓ የመመረጥ መብት በፍርድ ቤት ተገድቧል
- ✓ የድጋፍ ፊርማ የተጭበረበረ ነው ወይም በቂ የድጋፍ ፊርማ አላቀረበም

ከዕጩ ምዝገባ የቀጠለ

ፍርድ ቤት የሚሰጠው ውሳኔ

- ☞ ዕጩው እንዲመዘገብ ማድረግ
- ☞ ከዕጩዎች መዝገብ እንዲሰረዝ ማድረግ

ከዕጩ ምዝገባ የቀጠለ

ፍርድ ቤት የሚሰጠው ውሳኔ

- ☞ ዕጩው እንዲመዘገብ ማድረግ
- ☞ ከዕጩዎች መዝገብ እንዲሰረዝ ማድረግ

የዕጩዎች መለያ ምልክት

የሕግ መሰረቱ

- ☞ የዓለም አቀፍ ሰብአዊ መብት ኮንቬንሽን አንቀጽ 25
- ☞ ኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 38 (1)
- ☞ አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 37-38
- ☞ ለምዝገባ የሚቀርብ የዕጩ መለያ የምርጫ ምልክት፡-

- ✓ በብሔር ብሔረሰቦች ፣ በዘር፣ በሃይማኖት መካከል ጥላቻና ግጭት ይቀሰቅሳል
- ✓ የጦርነት ወይም የሌላ ሕገወጥ ድርጊት መልዕክት ያስተላልፋል
- ✓ ከፌደራልም ሆነ ከክልል መንግሥታት ሰንደቅ ዓላማ፣ አርማ ወይም ከልዩ ልዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ዓርማና ሰንደቅ አላማ ወይም ከሃይማኖት ድርጅቶች ምልክቶች ጋር ይመሳሰላል ወይም

የዕጩዎች መለያ የቀጠለ

- ✓ የሕዝብን ሞራል ወይም መልካም ስነ ምግባር ይጥሳል ወይም
- ✓ በምልክት ቋንቋ የታወቀ የተለየ ትርጉም አለው በሚል እንዳይመዘገብ ተከልክያለሁ ወይም ምልክቱን እንድቀይር ታዝዣለሁ በማለት አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

አቤቱታ ማቅረብ የሚችለው

የዕጩዎች መለያ የቀጠለ

አቤቱታ የሚቀርብባቸው ምክንያቶች

- ☞ ማንኛውም የግል እጩ ወይም የፓለቲካ ፓርቲ
- ✓ የምርጫ መወዳደሪያ ምልክቴ ያለአግባብ በሌላ ተወዳዳሪ ተወሰደብኝ ወይም
- ✓ በመረጥኩት ምልክት እንዳልጠቀም ተከለከልኩ
- ✓ እንድቀይር ታዘዝኩ

የዕጩዎች መለያ የቀጠለ

ፍርድ ቤት የቦርዱን ውሳኔ ሊያጸና ወይም ሊሽር ይችላል።

ፍርድ ቤቱ ውሳኔውን የሻረው እንደሆነ

- ✓ አመልካቹ ተወስዶብኛል በማለት አቤቱታ ያቀረበበት እና ለሌላ ሰው የተሰጠው የመለያ ምልክት እንዲሰረዝ ወይም
- ✓ አመልካች እንዳይጠቀም የተከለከለው የምርጫ መለያ ምልክት እንዲሰጠው ወይም
- ✓ የአመልካቹን የምርጫ መለያ ምልክት እየተጠቀመ ያለው ሰው መጠቀሙን እንዲያቆም ወይም
- ✓ አመልካች መለያ ምልክቱን እንዲቀይር ሊገደድ አይገባም ወይም ሊቀይር ይገባል በማለት ሊወሰን ይችላል።

በመራጮች ምዝገባ ሂደት ስለሚነሱ ክርክሮች

የመብቱ መሰረት፦

- ICCPR Art. 25፤ African charter፤ የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 38 (1) መሠረታዊ የመምረጥ መብት የተቀመጠ ሲሆን
- በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 /ከዚህ በኋላ አዋጁ እየተባለ የሚጠቀስ/ ከአንቀጽ 18-29 ስለ መራጮች መብት እና ስለመራጮች ምዝገባ ስርዓት ዝርዝር ድንጋጌዎችን አስቀምጧል
- በአዋጁ አንቀጽ 152 ደግሞ ከመራጮች ምዝገባ ጋር የተያያዙክርክሮችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ተካተዋል
- በምርጫ ቦርድ የወጡ የተለያዩ መመሪያዎች ከመራጮች ምዝገባ ጋር በተያያዘ ለሚነሱ ክርክሮች መሠረቶች ናቸው።

በመራጮች ምዝገባ የቀጠለ

አቤቱታ የማቅረብ መብት /Legal standing/

- ማንኛውም ለመራጭነት ከመመዝገብ የተከለከለ ሰው አንቀጽ 152 (1)
- መመዝገብ የሌለበት ሰው አላግባብ ተመዝግቧል የሚል ተቃውሞ ያለው ሰው ወይም የፖለቲካ ድርጅት (አንቀጽ 152 (2))
- በተጨማሪም የምርጫ ጉዳዮች በፍ/ቤት የሚስተናገዱበት ስነ ስርዓት እና የማስረጃ ረቂቅ ደንብ /ከዚህ በኋላ ረቂቅ ደንቡ እየተባለ የሚጠቀስ/ አንቀጽ 5 ላይም ተቀጧል

የአቤቱታው ምክንያቶች

- በመራጭነት ለመመዝገብ መስፈርቱን ባሟላም አላግባብ ከመመዝገብ ተከልክያለሁ (በአዋጁ አንቀት 18 (1))
- ከአመዘጋገብ ስህተት ጋር በተያያዘ የመራጭነት መብትን የሚያሳጣ ተግባር መፈጸም (በአዋጁ አንቀጽ 22)
- ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የመመዝገቢያ ቀን ሲያልፍ (በአዋጁ አንቀጽ 19 (3) እና (4) ፤ ስለ መራጮች ምዝገባ በምርጫ ቦርድ በወጣው መመሪያ አንቀጽ 10)
- ለመራጭነት ሊመዘገብ የማይገባው ሰው ከተመዘገበ
- በመራጭነት የተመዘገበው ሰው በህይወት አለመኖር
- ለመራጭነት ከመመዝገብ ከሚከለክሉ ምክንያቶች ቢያንስ አንዱን ያሟላ (በአዋጁ አንቀጽ 18 (3))
- የተመዘገበው ሰው በተጭበረበረ መንገድ ወይም ከአንድ በላይ የምርጫ ጣቢያ በመራጭነት ሲመዘገብ (በአዋጁ አንቀጽ 24)

አቤቱታውን ለማየት ስልጣን ስላለው አካል

- አቤቱታውን በመጀመሪያ ደረጃ ተቀብሎ የሚያስተናግደው
- የምርጫ ጣቢያ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ነው (በአዋጁ አንቀጽ 152 (1) (2) እና አንቀጽ 27)
- በምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴበሰጠው ውሳኔ ያልተስማማ ወይም ኮሚቴው በተቀመጠው ጊዜ ገደብ ወስጥ ውሳኔ ሳይሰጥ ቢቀር አቤቱታ አቅራቢው ቅሬታውን ለምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ማቅረብ ይችላል
- (በአዋጁ አንቀፅ 152 (5))
- በምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ ያልተስማማ ወይም የምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው በተቀመጠው ጊዜ ገደብ ወሳኔ ሳይሰጥ ቢቀር ቅሬታውን ስልጣን ላለው ፍ/ቤት ቅሬታ ያቀርባል (በአዋጁ አንቀጽ 152 (8))
- ጉዳዩ አዲስ አበባ እና ድሬ ዳዋ ከሆነ ፡- ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት (ረቂቅ ደንቡ አንቀጽ 5)
- ጉዳዩ በክልል ከሆነ፡- በወረዳ ፍ/ቤት (ረቂቅ ደንቡ አንቀጽ 5)
- ፍ/ቤቱ የሚሰጠው ውሳኔ (ይግባኝ የማይባልበት) የመጨረሻ ይሆናል (በረቂቅ ደንቡ አንቀጽ 52)

የማስረዳት ኃላፊነት

- አቤቱታ አቅራቢው አቤቱታውን የማስረዳት ግዴታ አለበት
- የማስረጃ አሰማም ሂደትን በተመለከተ ሊቅርቡ የሚችሉት ሠነዶች፤ የሰው ምስክር (ደንቡ አንቀጽ 40)

አቤቱታው የሚታይበት የጊዜ ሰሌዳ

- ለምርጫ ጣቢያ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜ

ከመራጮች የምዝገባ ቀን ጀምሮ የመራጮች መዝገብ ለህዝብ ይፋ የሚሆንበት ጊዜ እስከሚያልቅበት ጊዜ ድረስ (በአዋጁ አንቀጽ 152 (3))

- የምርጫ ጣቢያ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታ ሲቀርብለት በ5 ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት

የቀጠለ

ለምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አቤቱታ ለማቅረብ

- የምርጫ ጣቢያ ኮሚቴው ውሳኔ በሰጠ ወይም ውሳኔ የመስጫ ጊዜው ካለፈበት ቀን ጀምሮ እስከ 5 ቀን ድረስ (አዋጁ አንቀጽ 152 (6))
- የምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ የሚሰጠው በ5ቀናት ውስጥ መሆን አለበት (152(7))
- በምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚው ኮሚቴው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ሰው ውሳኔው በተሰጠ ወይም የመወሰኛ ጊዜው ካለፈበት ጊዜ ጀምሮ በ5 ቀናት ውስጥ ቅሬታውን እንደ አግባብነቱ ለክልል ወረዳ ፍ/ቤት ወይም ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ያቀርባል

በረቂቅ ደንቡ መሠረት

- ቅሬታ የቀረበለት ፍ/ቤትም ጉዳዩን ወደ ክርክር የሚያስገባ በቂ ምክንያት ካላገኘ አቤቱታውን ይሠርዘዋል።
- ፍ/ቤቱ መልስ የሚያሰጥ ሆኖ ካገኘው ተጠሪ መጥሪያ በደረሰው ከ48 ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ መልሱን ያቀርባል (በረቂቅ ደንቡ አንቀጽ 8)
- ፍ/ቤቱ ለቀረበለት አቤቱታ በ 4 ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት የሚጠበቅበት ሲሆን በማናቸውም ሁኔታ አቤቱታው ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ በ10 ቀናት ውስጥ (በረቂቅ ደንቡ አንቀጽ 9(1))

የሚሰጡ መፍትሄዎች

- አቤቱታ አቅራቢው በመራጭነት እንዲመዘገብ
- የአመዘጋገብ ስህተት እንዲስተካከል
- ከመራጭነት እንዲሠረዝ
- የስነ ምግበር ጥሰቶች እንዲታረሙ ለሚመለከተው አካል ጉዳዩን የማሳወቅ

ከመራጮች ምዝገባ ጋር በተያያዘ የወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስከትሉ ድርጊቶች

- የምርጫ ቁሳቁስ ማተም፤ ማባዛት፤ መፈብረክ፤ ማዘጋጀት፤

እና የተዘጋጀን ህገ ወጥ የምርጫ ሰነድ እና ቁሳቁስ ይዞ መገኘት ወይም ማደል (በአዋጁ አንቀጽ 157 (1))

- በቦርድ ወይም የምርጫ አስፈፃሚነት ገለልተኛነት ላይ ጣልቃ ለመግባት መሞከር በተለይም መደለያ ወይም ተስፋ ቃል መስጠት ወይም ለመስጠት መሞከር (በአዋጁ አንቀጽ 157 (3) (ሀ))
- ሆነ ብሎ የምርጫ ተቋሙን ኃላፊዎች ወይም ተግባር እና ኃላፊነቱን በሚያከናውኑበት ወቅት እንቅፋት መሆን ወይም ማወክ (አንቀጽ 157 (4) (ሀ))
- የወንጀል ህጉ አንቀጽ 470፡- በአመዘጋገብ ላይ የሚፈጠር ማጭበርበር

በድምፅ አሰጣጥ ሂደት ስለሚነሱ ክርክሮች

የመብቱ የህግ መሠረት

- ICCPR Art. 25፤ African charter፤ የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 38 (1) መሠረታዊ የመምረጥ መብት የተቀመጠ ሲሆን
- አዋጅ ቁጥር 1162/2011 ከአንቀጽ 18 እና አንቀጽ 47 - 56 እና አንቀጽ 154
- በምርጫ ቦርድ የወጡ የተለያዩ መመሪያዎች

በድምፅ አሰጣጥ ሂደት ስለሚነሱ ክርክሮች የቀጠለ

አቤቱታ የማቅረብ መብት /Legal standing/

- ከመምረጥ የተከለከለ የተመዘገበ መራጭ(አንቀጽ 154 (1))
- አንድ ሰው ሊመርጥ አይገባም በሚል የሚቃወም ማንኛውም ሰው (አንቀጽ 154 (5)
- የእጩ ተወካይ (አንቀጽ 54 (1)፤ (2)

በድምፅ አሰጣጥ ሂደት ስለሚነሱ ክርክሮች የቀጠለ

የአቤቱታ ምክንያቶች

- በመራጭነት ለመሳተፍ ወይም ለመምረጥ መከልከል (አንቀጽ 154 (1))
- ሌላ ሰው ሊመርጥ አይገባም በሚል ተቃውሞ ማቅረብ
- ምርጫ አስፈፃሚዎች በምርጫ ጣቢያው ድምፅ በሚሰጥበት ወቅት ተገቢ ያልሆነ ድርጊት (በአዋጁ አንቀጽ 54 (3)

አቤቱታውን ለማየት ሥልጣን ያለቸው አካላት

- አቤቱታውን በመጀመሪያ ደረጃ ተቀብሎ የሚያስተናግደው የምርጫ ጣቢያ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ (በአዋጁ አንቀጽ 154 (1)
- በምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወይም በተቀመጠው ጊዜ ገደብ ወስጥ ውሳኔ ያላገኘ ቅሬታውን ለምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ያቀርባል (በአዋጁ አንቀፅ 154 (3)
- በምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ ያልተስማማ ወይም በተቀመጠው ጊዜ ገደብ ወሳኔ ያላገኘ ስልጣን ላለው ፍ/ቤት ቅሬታ ያቀርባል (አንቀጽ 154 (4)) እና

በረቂቅ ደንቡ አንቀጽ 21 መሠረት

- ጉዳዩ አዲስ አበባ እና ድሬ ዳዋ ከሆነ ፡- በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት

ጉዳዩ ክልል ከሆነ፡- በወረዳ ፍ/ቤት

- ፍ/ቤቱ የሚሰጠው ውሳኔ (ይግባኝ የማይባልበት) የመጨረሻ ይሆናል (በረቂቅ ደንቡ አንቀጽ 52)

የማስረዳት ኃላፊነት

- አቤቱታ አቅራቢው አቤቱታውን የማስረዳት ግዴታ አለበት
- የማስረጃ አሰማም ሂደትን በተመለከተ ሊቅርቡ ሠነዶች፤ የሰው ምስክር (በረቂቅ ደንቡ አንቀጽ 40)

አቤቱታው የሚታይበት የጊዜ ሰሌዳ

ለምርጫ ጣቢያ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አቤቱታ ማቅረቢያ

- ከመምረጥ የተከለከለ ሰው አቤቱታውን ወዲያውኑ ለምርጫ ጣቢያ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ያቀርባል (በአዋጁ አንቀጽ 154 (1))
- የምርጫ ጣቢያ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው ውሳኔ የሚሰጥበትን ጊዜ በተመለከተ - የድምፅ መስጫ ጊዜው ከመጠናቀቁ በፊት ውሳኔ መስጠት አለበት (በአዋጁ አንቀጽ 54 እና 154 (2))
- በምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ ያልተስማማ ወዲያውኑ ለምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው ያቀርባል

የቀጠለ

- የክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴውም የምድፅ መደመሩ ከመጠናቀቁ በፊት መወሰን አለበት
- በምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ውሳኔ ያልተስማማ ወገን ወዲያውኑ ወይም በ24 ሰዓት ውስጥ ቅሬታውን ለፍ/ቤት ያቀርባል (ረቂቅ ደንቡ አንቀጽ 21 (1))

በረቂቅ ደንቡ መሠረት

- ቅሬታ የቀረበለት ፍ/ቤትም ጉዳዩ ወደ ክርክር ለመግባት በቂ ምክንያት ካላገኘ አቤቱታውን ይሠርዘዋል።
- መልስ የሚያሰጥ ሆነ ካገኘው ጉዳዩ የሚያገባው ሰው ወይም ተጠሪው መጥሪያ በደረሰው ከ24 ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ መልሱን ያቀርባል (በረቂቅ ደንቡ አንቀፅ 23 (2))
- ፍ/ቤቱ የድምፅ መደመሩ ሂደት እንዳይጀምር፤ ከተጀመረም እንዲቆም ሊያግድ ይችላል (አንቀጽ 154 (4) እና ረቂቅ ደንቡ አንፅ 24)
- ፍ/ቤቱ ውሳኔ የሚሰጥበት ጊዜ 3 ቀን ወይም እጅግ ቢዘገይ የድምፅ ማዳመሩ ከመጠናቀቁ በፊት (አዋጁ አንቀጽ 154 (3) እና ረቂቅ ደንቡ አንቀጽ 25(1))

የሚሰጡ መፍትሄዎች

- ድምፅ እንዲሰጥ፤ እንዲመርጥ
- ከመምረጥ እንዲከለከል
- የምርጫ አስፈፃሚው፤ የእጩ ተወካይ ወይም የሌላ ሰው ያልተገባ ድርጊት እንዲስተካከል፤ እንዲታረም
- ጊዜአዊ ድምፅ እንዲሰጥ ማድረግ (በአዋጁ 154 (2) (ለ))
- የስነ ምግባር ካለ እንዲታረም ለሚለከተው አካል መምራት

ከድምፅ አሰጣጥ ሂደት ጋር በተያያዘ የወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስከትሉ ድርጊቶች

- በድምፅ መስጫ እለት የፖለቲካ እንቅስቃሴ ማድረግ፤ መሣተፍ፤ ባልተገባ ወይም በተከለከለ ጊዜ የምርጫውን ውጤትን ማተም ወይም ማባዛት (አንቀጽ 157 (2))
- የምርጫ ምስጢራዊነትን መጣስ (በአዋጁ አንቀጽ 157 (3) (ሐ)
- ከድምፅ እና ከምርጫ ቁሳቁስ ጋር የተያያዙ ክልከላዎችን መተላለፍ (በአዋጁ አንቀጽ 157 (3) (መ))
- የወንጀል ህጉ አንቀጽ 467፡- የምርጫ ድምፅ የመስጠትን ወይም የመምረጥን መብት መንካት
- የወንጀል ህጉ አንቀጽ 471 በድምፅ አሰጣጥ ጊዜ የሚፈፀም የማጭበርበር ድርጊት

የድምጽ ቆጠራና ዉጤት አገላለጽ ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ክርክሮች

የመብቱ ህግ መሰረት

ዓለምአቀፍ መመዘኛዎች/መርሆዎች/International standards

ዓለም አቀፍ የሲቭልና ፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን ሰነድ/

ICCPR General Comment 25, para 20, “there should be independent scrutiny of the voting and counting process and access to judicial review …. so that electors have confidence in the …. counting of the votes”

African Charter on Democracy, Elections and Governance, Art. 17, “ensure that there is a binding code of conduct …. [that] includes a commitment by political stakeholders to accept the results of the election or challenge them through exclusively legal channels”

አገራዊ ሕግጋት/National Laws

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት

አንቀጽ 38 - የመምረጥና የመመረጥ መብት

ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ምንም አይነት ልዩነት ሳይደረግበት በመምረጥና በመመረጥ ሕዝባዊ ተሳትፎ የማድረግ መብት አለዉ፡፡

አዋጆች/ Legislation

- የኢትዮጵያ ምርጫ ፣፣የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነ ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011

ምእራፍ አምስት የድምጽ ቆጠራና ዉጤት አገላለጽ ስርዓት ከአንቀጽ 57-60 የድምጽ ቆጠራ ሂደት (ቦታ አጀማመርና ሂደት) ከአንቀጽ 61-62 የድምጽ ቆጠራ ዉጤት አገላለጽ ስርዓት አንቀጽ 155በድምጽ ቆጠራና ውጤት ስለሚነሱ ክርክሮች አመራር

- አዋጅ ቁጥር 1133/2011 የቦርዱ አካላት ሥልጣንና ተግባራት እና የፍርድ ቤቶች ሥልጣን

ደንብ /Regulation

የምርጫ ጉዳዮች በፍርድ ቤት የሚስተናገዱበት የሥነ ሥርዓት እና የማስረጃ ረቂቅ ደንብ

ምእራፍ ሰባት፡- ድምጽ ቆጠራ ሂደትና ውጤት የሚመለከቱ አቤቱታዎች አቀራረብ እና ውሳኔ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት

ምዕራፍ አምስት፡- የስነ ምግባር ጥሰቶች በሚመለከት የአቤቱታዎች አቀራረብ እና ውሳኔ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት

መመሪያዎች /Directives

የድምጽ አሰጣጥ፣የድምጽ ቆጠራ እና የዉጤት አገላለጽ ስርዓት መመሪያ

ከምርጫ ክልል ዉጭ የሚኖሩ ሰዎች እንደ ተማሪዎች፣የመከላከያ ሠራዊት አባላት እና በአገር ዉስጥ የተፈናቀሉ ሰዎች የሚመርጡበትን ልዩ የምርጫ ጣቢያ የሚመለከት መመሪያ (Directive on Special Polling Stations for people living outside their constituencies, such as students, members of the military and internally displaced people)

የድጋሚ ምርጫ ሥርዓት ሂደት የሚመራበት መመሪያ Directive on Re-election

ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አደራጀጀትና ቅሬታ የሚሰማበት ስርዓት መመሪያ

የድምጽ ቆጠራና ዉጤት አገላለጽ ተግባራት ሲከናወኑ ከላይ የተመለከቱትን ዓለም አቀፍ እና አገራዊ ሕግጋት ላይ የተመለከተዉን ባገናዘበ መልኩ ሊፈጸሙ ይገባል።

የድምጽ ቆጠራ እና ውጤት አገላለጽ

- ቆጠራ በምርጫ ጣቢያ ይከናወናል፤(አ/ቁ 1162/2011 አንቀጽ 57/1)
- ለሕጉ የተመለከተዉ ልዩ ሁኔታ ሲያግጥም ፡- በምርጫ ክልሉ ጽ/ቤት ይካሄዳል አንቀጽ 57/2
- ለቆጠራ ቦታ መገኘት ስላለባቸዉ ሰዎች እና ቆጠራ የሚደረግበት ቦታ በቂ የተፈጥሮ ወይም ሰዉ ሰራሽ ብርሃን የሚያስፈልግ ስለመሆኑ አንቀጽ 57/3 እና 58(1)

የድምጽ ቆጠራ አጀማመርና ሂደት (አንቀጽ 58)

☞ የድምጽ መስጫ ሳጥን እሸግ የሚከፈተው ተገቢው ስርዓት ከተሟለ በኃላ ነው

☞ በድምጽ ቆጠራ ወቅት ዋጋ ያላቸዉ የድምጽ መስጫ ወረቆቶች ዋጋ ተሰጥቷቸዉ የሚቆጠሩበትን ስርዓት እና ዋጋ አልባ ወረቀቶች ዉድቅ የሚደረጉበት ስርዓት (በአዋጁ አንቀጽ 58-59 ተመልክቷል)

☞ የደምጽ ቆጠራ ሲጠናቀቅ ቆጠራዉ መጠናቀቁ የሚረጋገጥበት ሥርዓት (በአዋጁ አንቀጽ 60

☞ የድምጽ ቆጠራ እንደተጠናቀቀ ተገቢው ስርዓት ተከናውኖ ውጤት በምርጫ ጣቢያዊ በ1 ሰዓት ውስጥ፣ በምርጫ ክልል በ5 ቀናት በቦርድ ደረጃ በ10 ቀናት ውስጥ ይለጠፋል፣ በልዩ ሁኔታ 20 ቀናት(አንቀጽ 61-62)

ድምጽ ቆጠራ ሂደትና ውጤት የሚመለከቱ አቤቱታዎች አቀራረብ እና ውሳኔ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት

- ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ወይም የግል እጩ ወይም ወኪል (አዋጅ ቁ. 1162/2011 አንቀጽ 155/1 ፣118-119 ፣ 58/6 እና ረቂቅ ደንብ አንቀጽ 26)

አቤቱታ ስለሚቀርብባቸው ምክንያቶች/ Grounds for complaint ፡-

የሚቀርበዉ አቤቱታ መሰረታዊ የመምረጥና የመመረጥ መብት ለማስከበርና እዉነተኛና ተአማንነት ያለዉን የምርጫ ሂደትና ዉጤት ለማረጋገጥ የሚያስችል መሆን አለበት፡፡

- በአዋጁ አንቀጽ 57 እስከ 61 (በተለይ 59 እና 60 ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (3) ፣62(1/ረ) የተመለከቱትን እና በአዋጁ ሌሎች ድንጋጌዎች የተገለጹ ምክንያቶችን የሚያካትቱ ይሆናሉ፡፡
- **ለምሳሌ ፡- ያለቦታዉ ቆጠራ ማከናወን ፣ዋጋ አልባ የሆኑ እና ጥቅም ላይ ያልዋሉ ወይም የተበላሹ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ተቆጥረዋል፣**
- **በአግባቡ የተሰጠ ድምጽ ዋጋ አልባ ሆኗል፣**
- **የድምጽ መቆጠሩ እና ማዳመሩ ወቅቱን እና ሥርዓቱን ጠብቆ አልተከናወነም፣**
- **የምርጫዉ ውጤት ለህዝብ ይፋ ሳይደረግ አለአግባብ ዘግይቷል (የረቂቅ ደንቡ አንቀጽ 27 ይመልከቱ)**

ድምጽ ቆጠራ ሂደትና ውጤት የሚመለከቱ አቤቱታዎች አቀራረብ እና ውሳኔ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት

አቤቱታ ለማቅረብ መብት ያለው/Legal standing፡-

- ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ወይም የግል እጩ ወይም ወኪል (አዋጅ ቁ. 1162/2011 አንቀጽ 155/1 ፣118-119 ፣ 58/6 እና ረቂቅ ደንብ አንቀጽ 26)

አቤቱታ ስለሚቀርብባቸው ምክንያቶች/ Grounds for complaint ፡-

የሚቀርበዉ አቤቱታ መሰረታዊ የመምረጥና የመመረጥ መብት ለማስከበርና እዉነተኛና ተአማንነት ያለዉን የምርጫ ሂደትና ዉጤት ለማረጋገጥ የሚያስችል መሆን አለበት፡፡

- በአዋጁ አንቀጽ 57 እስከ 61 (በተለይ 59 እና 60 ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (3) ፣62(1/ረ) የተመለከቱትን እና በአዋጁ ሌሎች ድንጋጌዎች የተገለጹ ምክንያቶችን የሚያካትቱ ይሆናሉ፡፡
- **ለምሳሌ ፡- ያለቦታዉ ቆጠራ ማከናወን ፣ዋጋ አልባ የሆኑ እና ጥቅም ላይ ያልዋሉ ወይም የተበላሹ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ተቆጥረዋል፣**
- **በአግባቡ የተሰጠ ድምጽ ዋጋ አልባ ሆኗል፣**
- **የድምጽ መቆጠሩ እና ማዳመሩ ወቅቱን እና ሥርዓቱን ጠብቆ አልተከናወነም፣**
- **የምርጫዉ ውጤት ለህዝብ ይፋ ሳይደረግ አለአግባብ ዘግይቷል (የረቂቅ ደንቡ አንቀጽ 27 ይመልከቱ)**

የዳኝነት ሥልጣን /Jurisdiction

የድምጽ ቆጠራ ሂደትና ዉጤት ጋር በተያያዘ አቤቱታ ተቀብለዉ ዉሳኔ የሚሰጡ አካላት፦

- በየደረጃዉ ያሉ ቅሬታ ሰሚ አካላት(አንቀጽ 58/6፣፣155(1 እስከ 3)

- የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፦-በቦርዱ ውሳኔ በተሰጠ በ10 ቀናት ውስጥ ቅሬታ ካለ ሊቀርበለት ይችላል።(155(4)

- የሥራ አመራር ቦርድ የምርጫ ሂደትና ዉጤትን በተመለከተ የሚሰጣቸዉ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ዉሳኔ ከተሰጠ በኋላ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ በይግባኝ በአቤቱታ ቀርቦ ይወሰናል። (አዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 17/1 እና አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 155/4 ይመለከቷል።)

- ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በይግባኝ/አቤቱታ አይቶ የሚሰጠዉ ዉሳኔ የመጨረሻ ይሆናል (ረቂቅ ደንብ አንቀጽ 52)።

- ሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80(3/ሀ) መሰረት መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚል አቤቱታ ለሰበር የሚቀርብ መሆኑ የተጠበቀ ነዉ።

ድምጽ ቆጠራ ሂደትና ውጤት የቀጠለ

ዉሳኔ የሚሰጥበት ጊዜ/Timeline

-አቤቱታ ከቀረበለት ጊዜ ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ዉሰጥ ዉሳኔ መስጠት ይኖርበታል።(አዋጅ ቁ.1162/2011 አንቀጽ 155/5 ፣ አዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 17/2)

ዯምርጫው ሂደት ነፃ፣ ፍትሀዊ፣ ዴሞክራሲያዊና ሰላማዊ ሆኖ እንዲቀጥል ለማስቻል የምርጫውን የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በማድረግ መቀበልና አፋጣኝ ውሳኔ መስጠት አለበት። (አዋጅ ቁ. 1162/2011 አንቀጽ 151/6 እና ረቂቅ ደንብ አንቀጽ 45)

ድምጽ ቆጠራ ሂደትና ውጤት ቀጠለ

የማስረጃ አቀራረብና ምዘና ሥርዓት Production,Standard and Burden of proof

ብፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አግባብ የሚታይ(ረቂቅ ደንብ አንቀጽ 56)

✓ የድምጽ ቆጠራ ሂደቱን እና/ወይም ዉጤቱን ትክክል አይደለም ብሎ የሚከራከር ወገን በቅድሚያ አግባብነት ባለዉ ማስረጃ የማስረዳ ግዴታ ይኖርበታል።

❖ሚከተሉት ማስረጃዎች አግባብነት ያላቸዉ ናቸዉ። ለምሳሌ፦

ቀምርጫ ጣቢያና የምርጫ ክልል ቃለ ጉባኤ

ቀድምጽ ቆጠራ ዉጤት የተመዘገበበት ሰነድ

ቀድምጽ ቆጠራና ዉጤት ሲገለጽ የተከሰተ ሥነ ሥርዓታዊ ያልሆነ ተግባራት የሚያሳይ ፎቶግራፍ ወይም ቪዲዮ እና ምስክሮችየምርጫ አስፈጻሚዎች እና ሌሎች የአይቲ ባለሙያዎች ...

ድምጽ ቆጠራ ሂደትና ውጤት ቀጠለ

ፍርድ ቤቱም የቀረበለትን ይግባኝ ለመወሰን የሚያስፈልጉ ማስረጃዎችን አስቀርቦ መመርመር ይችላል። (አዋጅ ቁ.1162/2011 አንቀጽ 155/4)

ክርክር የሚመራበት ሥነ ሥርዓት/Procedure

ብአዋጆቹ የተመለከቱ ሥነ ሥርዓታዊ ድንጋጌዎች

ረቂቅ የስነ ሥርዓትና ማስረጃ ደንብ(ሲጸድቅ)

ከላይ በተጠቀሱ ሕጎች ያልተሸፈኑትን ጉዳዮች በተመለከተ የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕጉ ተፈጻሚ ይሆናል።

ድምጽ ቆጠራ ሂደትና ውጤት ቀጠለ

የሚሰጠዉ ዉሳኔ ይዘት/Remedies

ብድምፅ ቆጠራ ሂደትና በውጤቱ ላይ የቀረበ ይግባኝ ከሆነ ይግባኙ በሚሰማበት ጊዜ እንደአግባብነቱ የፊዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቅሬታ የቀረበበት የምርጫ ክልል ውጤት እንዳይገለጽ ጊዜያዊ እግድ ሊሰጥ ይችላል።

(አዋጅ ቁ. 1162/2011 አንቀጽ 155/6 ረቂቅ ደንብ አንቀጽ 26)

የቦርዱን ውሳኔ ሊያጸናዉ፣ሊያሻሽለዉ ወይም ሊሽረዉ ይችላል።

ዉጤቱም እንደነገሩ ሁኔታ፣ -

ችቤቱታው በጊዜ ካልቀረበ በይርጋ የሚታገድ መሆኑ (አዋጅ ቁ. 1162/2011 አንቀጽ 151/13)

ችቤቱታው መነሻ ምክንያት የሌለው እንደሆነ አቤቱታውን ይሰርዘዋል።(የረቂቅ ደንቡ አንቀጽ 33/3)

ችግዱን በማንሳት አቤቱታ የተነሳበት የምርጫ ጣቢያ ወይም የምርጫ ክልል ውጤት ለሕዝብ እንዲገለጽ ፣

ድምጽ ቆጠራ ሂደትና ውጤት ቀጠለ

የምርጫ ዉጤትን የሚያዛንፍ የህግ ጥሰት በተከሰተ ጊዜ አቤቱታ የተነሳበት የምርጫ ጣቢያ ወይም የምርጫ ክልል ውጤት በሙሉ ወይም በከፊል እንዲሰረዝ፣

-ዳግም ቆጠራ እንዲካሄድ ወይም ፣

ድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ ሊወስን ይችላል።

(አዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 7/20 እና 8/4፣ አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 10/1 እና ረቂቅ ደንብ አንቀጽ 30)

የምርጫ ሰነ ምግባር ጥሰቶችን እና ምርጫ ነክ ወንጀሎችን አሰመልክቶ ስለሚቀርብ አቤቱታ

1) የአቤቱታ ማቅረቢያ ሕጋዊ መሰረቶች

ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸው አለም አቀፍ እና አሕጉራዊ የሰብአዊ መብት ሰነዶች፡

አለም አቀፍ የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች ኮቫነንት (ICCPR) አ. 2(2) ፤ አገራት በኮቫነንቱ ውስጥ ያሉ መብቶች ተፈጻሚ እንዲሆኑ ሕጎችን ወይም ሌሎች አስፈላጊ እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው።

አ. 19፤ የመናገርና ሃሳብን የመግለጽ ነጻነት... ፣

አ. 20(2)፤ ማንኛውም በዘር፣ በብሄር፣ በዜግነት፣ ወይም በሃይማኖት ላይ የተመሰረተ የጥላቻ ቅስቀሳ መድሎን፣ ጸብን ወይም ብጥብጥን የሚያነሳሱ በመሆናቸው የተከለከሉ መሆናቸው፤

አ. 21፡ የመሰብሰብ መብት የተከበረ ስለመሆኑና ብሄራዊ ወይም የህዘብ ደህንነት፣ የህዝብን ጤና ወይም ሞራል ወይም የሌሎች ሰዎችን መብት ለማክበር የሚያስፈልጉና በዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ ውስጥ ተገቢነት ያላቸው ገደቦች ብቻ ናቸው በዚህ መብት ላይ ሊጣሉ የሚችሉት።

የቀጠለ

- የአፍሪካ የህዝቦችና የሰዎች መብቶች ኮንቬንሽን (African Charter on Human and Peoples' Rights)
  - አ. 9፤ ማንኛውም ሰው በሕግ በተፈቀደ መጠን መረጃ የማግኘትና ሃሳቡን የመግለጽና የማሰራጨት መብት ያለው መሆኑ.
  - አ. 11፤ ማንኛውም ሰው ህጋዊ ገደቦችን በማከበር ከሌሎች ሰዎች ጋር በጋራ ሰላማዊ በሆነ መንገድ መሰብሰብ የሚችል መሆኑ
  - አ. 13(3) ማንኛውም ሰው በህዝብ(መንግስት) ንብረትና አገልግሎቶች ያለአድልኦና በእኩልነት የመጠቀም መብት ያለው መሆኑ
- African Charter on Democracy, elections and Governance)
  - አ. 17(4)፤ አገሮች በቅድመ ምርጫ፣ በምርጫ ወቅት እና ድህረ ምርጫ ጊዜ የሚያገለግሉ ለፖለቲካ ባለድርሻ አካላት፣ ለመንግስት እና ለሌሎች ተዋናዮች የሚያገለግሉ ገዢነት ያላቸው የስነ ምግባር ሰምምነቶች እንዲኖሩ ማድረግ ያለባቸው ስለመሆኑ፤

የቀጠለ

- የኢ.ፌ.ዴሪ ሕገ መንግስት
  - አ. 29 (1)፡ ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት የመሰለውን አመለካከት ለመያዝ የሚችል ስለመሆኑ
  - አ. 29(2)፤ ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት ሃሳቡን የመግለጽ ነጻነት አለው፤ ይህ ነጻነት ከሃገር ውጪም ሆነ በአገር ውስጥ ወሰን ሳይደረግበት በቃልም ሆነ በጽሁፍ ወይም በህትመት፣ በስነ ጥበብ መልክ ወይም በመረጠው በማንኛውም የማሰራጫ ዘዴ ማንኛውንም የማሰራጫ ዘዴ፣ ማንኛውንም አይነት መረጃና ሃሳብ የመሰብሰብ፣ የመቀበልና የማሰራጨት ነጻነቶችን ያካትታል።
  - አ. 29(6)፤ እነዚህ መብቶች ገደብ ሊጣልባቸው የሚችለው የሃሳብና መረጃ የማግኘት ነጻነት በአስተሳሰባዊ ይዘቱና ሊያስከትል በሚችለው አስተሳሰባዊ ውጤት ሊገታ አይገባውም በሚል መርህ ላይ ተመስርተው በሚወጡ ሕጎች ብቻ ይሆናል። የወጣቶችን ደህንነት፣ የሰውን ክብርና መልካም ስም ለመጠበቅ ሲባል ሕጋዊ ገደቦች በነዚህ መብቶች ላይ ሊደነገጉ የሚችሉ ስለመሆኑ እና የጦርነት ቅስቀሳዎች እንዲሁም ሰብኣዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎች በሕግ የሚከለከሉ ስለመሆኑ
  - አ. 29(7)፤ በነዚህ መብቶችን አጠቃቀም በተመለከተ የሚጣሉ ሕጋዊ ገደቦች መከበር ያለባቸው ስለመሆኑ...

የቀጠለ

አ. 30(1)፤ ማንኛውም ሰው ከሌሎች ጋር በመሆን መሳሪያ ሳይዝ በሰላም የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነጻነት እና አቤቱታ የማቅረብ መብት ያለው መሆኑ፣ በነዚህ መብቶች አጠቃቀም ሰላምን፣ ዴሞክራሲያዊ መብቶችንና የህዝብን የሞራል ሁኔታ እንዳይጥሱ ለማስጠበቅ አግባብ ያላቸው ስርዓቶች ሊደነገጉ የሚችሉ ስለመሆኑ፣

አዋጅ ቁ. 1162/2011፤

ከአ. 43፣ በምርጫ ወቅት የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ማካሄድ የሚቻል መሆኑን፤

አ. 44፣ በመንግሥት ቁጥጥር ስር ያሉትን መገናኛ ብዙኃን ማለትም ሬድዮ፣ ቴሌቪዥንና ጋዜጦችን ለምርጫ ዘመቻ ተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ያለ አድልዎ ነጻ የአየር ጊዜ የማግኘት መብትን ጨምሮ የመጠቀም መብት ያላቸው መሆኑን፣

አ. 45፤ የምርጫ ውድድር እንቅስቃሴዎችን ለማሳካት በየደረጃው የሚገኙ የመንግሥት አካላት ኃላፊዎች ግዴታ....

የቀጠለ

- አ. 127-141፡ የምርጫ ስነ ምግባርን የያዙ ድንጋጌዎች ናቸው።
  - አ. 129 የምርጫ ዘመቻ ፡ አካሄድ....
- አ. 142-150፤ የስነምግባር ጥሰቶችን፣ በባለደርሻ አካላት የሚወሰዱ እርምጃዎችን ይደነግጋሉ.....
- ቦርዱ በአዋጁ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ያወጣቸው መመሪያዎች፤
  - የምርጫ ዘመቻ እንቅስቃሴ ስነ ምግባር መመሪያ
  - የቦርዱ የአቤቱታ አወሳሰን ስርዓት መመሪያ
- 2) አቤቱታ የማቅረብ መብት፤
  - የምርጫ ስነ ምግባር ጥሰቶችን በሚመለከት አዋጁን መሰረት በማድረግ የምርጫ ዘመቻ እንቅስቃሴ ስነ ምግባር መመሪያ የቦርዱ የአቤቱታ አወሳሰን ስርዓት መመሪያ ላይ ማን አቤቱታ ማቅረብ ይችላል የሚለው ተመልክቷል፡
  - የፖለቲካ ፓርቲ፤ እጩ፣ የጥሰቱ ተጎጂ ወይም ማንኛውም ሌለ በጉዳዩ ላይ ጥቅም አለኝ የሚል ሰው ...

የቀጠለ

3/ የአቤቱታ ምክንያቶች፤

- በማንኛውም ፓርቲ፣ እጩ፣ የፓርቲ መሪ፣ የፓርቲ አባል፣ ወኪል፣ ወይም በማንኛውም ፓርቲን ወይም እጩን የሚወክል ሰው በምርጫ ዘመቻ ወቅት የስነ ምግባር ጥሰት ሲፈጸም ለቦርዱ አቤቱታ ሊቀርብ ይችላል (የምርጫ ዘመቻ እንቅስቃሴ ስነ ምግባር መመሪያ፣ አ. 21)፣
- ቦርዱ በራሱ ተነሳሽነት የስነ ምግባር ጥሰት ሰለመፈጸሙ ማጣራት ይችላል
- የምርጫ ዘመቻ ወቅት የሚጀምረው አንድ እጩ የእጩነት መታወቂያውን ካገኘበት ጊዜ ጀምሮ ሲሆን የሚጠናቀቀው የምርጫው ሰዓት 4 ቀናት ሲቀሩት ነው። የእጩዎች ምዝገባ ምርጫው ዘጠና ቀናት ሲቀሩት መጠናቀቅ እንዳለበት አዋጅ ቁ. 1162 አ. 30 ይደነግጋል፣

የቀጠለ

- ✓ አዋጅ ቁ. 1162 እና የምርጫ ዘመቻ እንቅስቃሴ ስነ ምግባር መመሪያው በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት ሊፈጸሙ የሚችሉ የስነ ምግባር ጥሰቶችን በዝርዝር ይደነግጋሉ፤
  - ✓ ከምርጫ ቅስቀሳ የጊዜ ሰሌዳ ውጭ ቅስቀሳ ማድረግ (አ. 43፤ መመሪያው አ. 15)
  - ✓ በተከለከሉ ቦታዎች የምርጫ ቅስቀሳ ማካሄድ (አዋጅ አ. 46)
  - ✓ በ አዋጁ አ. 129 ስለምርጫ ዘመቻ አካሄድ የተደነገጉትን መጣስ፣
  - ✓ ስለምርጫ ሂደት የተደነገጉ የስነ ምግባር ድንጋጌዎችን መጣስ (አዋጅ፣ አ. 130)
  - ✓ የምርጫ ውጤትን ስለመቀበል (አዋጅ፣ አ. 131)
  - ✓ ለምርጫ ዘመቻ ጥቅም ላይ ስለሚውል የቋንቋ ይዘት እና ሰላማዊነት ደንጋጌዎች (አዋጅ፣ አ. 132)

የቀጠለ

- ያልተገባ የምልክቶች አጠቃቀምን የሚከለክል የስነ ምግባር ድንጋጌ (አዋጅ፣ አ. 133)
- ማስፈራራትና አመጽ መቀስቀስ ክልክል ስለመሆኑ (አዋጅ፣ አ. 134)
- ስልጣንን ያለ አግባብ መጠቀም የሚመለከት የስነ ምግባር ድንጋጌ (አዋጅ፣ አ. 135)
- የሙስና ተግባርን የሚመለከት ድንጋጌ (አዋጅ፣ አ. 136)

የስነ ምግባር ጥሰቶች (ተጠያቂነት የሚያስከትሉ)

- መደለያ መስጠትና ኃይልን ወይም ሥልጣንን አለ አግባብ መጠቀም (አዋጅ አ. 142)
- ፍርሃት በመቀስቀስ ወይም ሁከት መፍጠር ማንኛውንም የምርጫ እንቅስቃሴ ማስተጓጎል (አዋጅ አ. 143)
- በምርጫ ሂደት ሰላምና ፀጥታ የሚያናጉ መልዕክቶችን ማስተላለፍ (አዋጅ አ. 144)
- የሌሎች የፖለቲካ ፓርቲ ወይም እጩ ተወዳዳሪዎች የምርጫ እንቅስቃሴ ማደናቀፍ (አዋጅ አ. 145)

የቀጠለ

- ከጋዜጠኞች ወይም ከታዛቢዎች ጋር አለመተባበር (አዋጅ አ. 146)
- የሥነ ምግባር ድንጋጌዎቹን አለማስተዋወቅና ሕገ ወጥ ድርጊቶችን አለማውገዝ (አዋጅ አ. 147)
- የመንግስትን ሃብት/ንብረት፣ የስራ ሰዓት ለምርጫ ዘመቻ እንቅስቃሴ አለማዋል (መመሪያ አ. 13)
- እነዚህ ድንጋጌዎች የምርጫ ጉዳዮች በፍ/ቤት የሚስተናገዱበት የስነ ስርዓትና የማስረጃ ደንብ (ረቂቅ) (አ. 18) ስር ቦርዱ በነዚህ አቤቱታዎች ላይ በሚወስነው ውሳኔ ቅሬታ ያለው ሰው ወይም የፖለቲካ ፓርተ በአዋጁ አ. 149 በተደነገገው መሰረት አቤቱታውን በ10 ቀናት ውስጥ ለፌ. ከ. ፍ/ቤት ማቅረብ እንደሚችልተመልክተዋል።

የቀጠለ

4/ ጉዳዩን የማየት ስልጣን

- ቦርዱ የስነ ምግባር ጥሰትን በሚመለከት አስተዳደራዊ እርምጃ መውሰድ የሚችል መሆኑ በአዋጁ ተደንግጓል፤
- በቦርዱ የአቤቱታ አወሳሰን ስርዓት መመሪያ መሰረት ከባድ የስነ ምግባር ጠሰት በመሆናቸው ወይም በስፋትና በብዙ ቦታዎች በመከሰታቸው ምክንያት ለቦርዱ በቀጥታ ማቅረብ ያለባቸው ካልሆኑ በስተቀር የምርጫ ክልል ጽ/ቤት የስነ ምግባር ጥሰት አቤቱታዎችን በመጀመሪያ ደረጃ አንዲወስን ስልጣን ተሰጥቶታል፤
- በ ምርጫ ክልል ጽ/ቤት በተሰጠ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን ለቦርዱ ማመልከት ይችላል (አዋጅ አ. 148፤ መመሪያዎች)
- በቦርዱ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ለፌ.ከ. ፍ/ቤት አቤቱታ ማቅረብ ይችላል (አዋጅ አ. 149፤ ደንብ አ. 18)
  - በፍ/ቤቱ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ነው (ደንብ፣ አ. 52)
- ከላይ የተመለከቱት የስነ ምግባር ጥሰቶች ወንጀል በሚሆኑበት ጊዜ ቦርዱ ጉዳዩን ለተገቢው አካል ይመራል፤ ይከታተላል።

የቀጠለ

5/ ስለማስረዳት ኃላፊነት ፣ ስለማስረጃ ምዘና

- ማንኛውም አመልካች ለሚያቀርበው ማመልከቻ በቂ ማስረጃ ሊያቀርብ ይገባል፣
- ቦርዱ በበቂ ማስረጃ ላይ ተመስርቶ የስነ ምግባር ጥሰቶችን በራሱ ተነሳሽነት ሊያጣራ ይችላል።ማስረጃዎች አይነት፤ የሰነድ፣ የድምጽ፣ የምስል፣ ፎቶግራፍ... የሰው ምስክር ሊሆን ይችላል
- የማስረጃ ምዘና ስርዓት በአገሪቱ ሌሎች ህጎች በተደነገገው መሰረት ነው፤
- የወንጀል ጉዳዮች የማስረጃ ምዘና ስርኣት በወንጀል ስነ ስርዓት ሕጎች በተሰጠው መሰረት ነው

የቀጠለ

6/ የጊዜ ገደብ

- ✓ ለምርጫ ክልል ጽ/ቤት የስነ ምግባር ጥሰት አቤቱታ ጥሰቱ በተፈጸመ በ5 ቀናት መቅረብ አለበት፤ ጽ/ቤቱ በ10 ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት (የቦርዱ የውሳኔ አሰጣጥ ሥ. ሥ ረቂቅ ደንብ)
- ✓ በምርጫ ክልል ጽ/ቤት ውሳኔ ቅር የተሰኘ አካል ለቦርዱ በ5 ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ማቅረብ አለበት፣ ቦርዱ በ10 ቀናት ውስጥ ውሰኔ መስጠት አለበት (የቦርዱ የውሳኔ አሰጣጥ ሥ. ሥ ረቂቅ ደንብ)
- ✓ በቦርዱ ውሳኔ ቅር የተሰኘ አካል ለፌ. ከ. ፍ/ቤት በ10 ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ማቅረብ አለበት፤ ፍ/ቤቱም በአ. 1133፣ 1162 እና በደንቡ መሰረት እጅግ ቢዘገይ በ30 ቀናት ውስጥ፣ ነገር ግን እንደነገሩ አጣዳፊነት በተገቢው ጊዜ ውሳኔ መስጠት አለበት።
- ✓ ለቦርዱ የሚቀርብ አቤቱታ የሚመራበት ስርዓት በቦርዱ የአቤቱታ አወሳሰን ስርዓት መመሪያ መሰረት ሲሆን ለከ. ፍ/ቤት የሚቀርብ አቤቱታ የምመራው በደንቡ መሰረት ነው።

የቀጠለ

7/ ስለሚሰጥ ዳኝነት

አስተዳደራዊ ዳኝነት፣ በቦርዱ የሚሰጠው፤ አዋጅ አ. 148፤ የምርጫ ዘመቻ እንቅስቃሴ ስነ ምግባር መመሪያ አ. 22፣

- ጥፋቱን ለፈፀመ ሰው ወይም የፖለቲካ ፓርቲ ይፋ ማስጠንቀቂያ መስጠት፤
- ጥፋቱን የፈፀመ እጩ ወይም ፓርቲ ለአጭር ጊዜ በከፊል ወይም በሙሉ በመገናኛ ብዙሃን እንዳይጠቀም ማገድ፤
- ጥፋቱን የፈፀመ ፓርቲ በመንግሥት ለፖለቲካ ፓርቲዎች ድጎማ ከሚመድበው ገንዘብ ፓርቲው ተጠቃሚ እንዳይሆን ማድረግ፤
- ጥፋተኛውን የፓርቲ ወይም የግል እጩ ተወዳዳሪ እንደጥፋቱ ክብደት ከምርጫ ተወዳዳሪነት መሰረዝ፤
- ጥፋተኛው የፖለቲካ ፓርቲው በምርጫ ውድድር እንዳይሳተፍ ማገድ።

የቀጠለ

- **8/ የወንጀል ድርጊቶች፡**
- **ቦርዱ ከላይ የተዘረዘሩትን ቅጣቶች በጥፋተኛው ላይ ከማስተላለፍ በተጨማሪ እንደ ጥፋቱ ሁኔታ ጉዳዩን ወደ ዓቃቤ ሕግ ሊመራው ይቻላል (አዋጅ አ. 148(5)፤** የምርጫ ዘመቻ እንቅስቃሴ ስነ ምግባር መመሪያ አ. 23) ።
- ከምርጫ ጋር የተያያዙ የወንጀል ድርጊቶች የሚከተሉት ናቸው፡
  - በአዋጁ አ. 157 የተመለከቱት የወንጀ፤ል ድርጊቶች
  - የምርጫ ማስታወቂያን ስለማጥፋት (አዋጅ አ. 158)
  - ዓላማን በህገወጥ መንገድ ማስፋፋት የተከለከለ ስለመሆኑ (አዋጅ አ. 159)
  - ለምርጫ የሚደረግ ስብሰባንና የምርጫ ሂደትን ማወክና ማሰናከል (የወንጀል ሕግ አ. 466)፤

የቀጠለ

- ✓ የምርጫ ድምጽ መስጠትን ወይም የመምረጥን መብት መንካት (የወንጀል ሕግ አ. 467)፤
- ✓ በምርጫ ላይ ስለሚሰጥ መደለያ ((የወንጀል ሕግ አ. 468)፤
- ✓ ስለማይገባ አሰራር (የወንጀል ሕግ አ. 469)፤
- ✓ በአመዘጋገብ ላይ ስለሚፈጸም ባጭበርበር (የወንጀል ሕግ አ. 470)፤
- ✓ በድምጽ አሰጣጥ ጊዜ የሚፈጸም የማጭበርበር ድርጊት ((የወንጀል ሕግ አ. 471)፤
- ✓ የድምጽ አሰጣጥ ሚስጢር አጠባበቅን መጣስ ((የወንጀል ሕግ አ. 473)፤
- ✓ የድምጽ መስጫ ወረቀቶችን እና የምርጫ ሳጥኖችን መውሰድና ማጥፋት (የወንጀል ሕግ አ. 474)::